## “መሐይምነት ለድፍረት ፍቅረ ንዋይ ለክኽደት ይመቻል[፩]”

መቼም የአንኮበር፣ የአድዋና የአንጎለላ ኪዳነ ምኅረት ስም ሲነሳ ምን ተፈጠረ እያለ ዛሬም በሰማይ ቤት ልጄ መጨነቁን አላቆመም። ቁልቁል እየተመለከተ ሁሌ ማዘንን ልማዱ ቢያደርገውም፣ እነዚህ ስሞች ሲጠሩ ሲሰማ ግን ያየውን እንኳን አላምን ብሎ የሚባለውን በተመስጠ እስከመጨረሻው ከማዳመጥ ቦዝኖ አያውቅም።

ባለፈው መጋቢት፣ በሕማማቱ፤ ያለወትሮው በጧት ከትንሿ ጎጆዬ በጸሎት ላይ ሳለሁ ጠራኝ። ለወትሮው ሕማማትን ስንኳን ሰው ሊያናግር ሹክሹክታ እንኳ ሲሰማ ፊቱን ይሸፍናል። ስለሐገሩ፣ ስለሕዝቡ፣ ስለወንዙ፣ ስለዋሻው፣ ስለተራራው፣ የሚያወርደውን ዕንባ ለአፍታ እንዳናቋርጥበትና እንዳናይበት። እናት ነኝና ዛሬም መደንገጤን አላቋረጥኩም፤ ሳየው ጸሎቴን አቋርጬ “ምነው ምን ሆንክ? ምን አገኘህ?” አልኩት።

“እንዳትደብቂኝ፤ ዕውነቱን ልትነግሪኝ ቃል ግቢልኝና እነግርሻለሁ” አለኝ።

“ልጄ፤ ከዚህ ቀደም የደበቅኹህ ወይንስ የዋሸኹህ ነበርን፤ እኔ ካንተ በቀር ምን ሀብት፣ ምን ክብር፣ ምንስ ሞገስ ኖሮኝ አደርገዋለሁ። ሕይወቴ፣ ክብሬ፣ ታሪኬ አንተ አይደለህምን፤ ምን አገኝ ብዬ እዋሽሃለሁ፤ ምንስ አተርፍ ብዬ እደብቅሃለሁ” አልኩት። በርግጥም ልጄን አንዲትም ቀን ዋሽቼው አላውቅም፤ ባይሆን ሌላ ቀን ብዬ አረሳሳዋለሁ እንጂ።

“ደስ የማያሰኝሽ ቢሆንስ ታዝኚብኛለሽ?” አለኝ መቼም ሲፈጥረው እርሱ ይጎዳል እንጂ ሰውን ማስከፋት አይሆንለት።

“ንጉሥን እኮ አስከፋኸኝ፣ አሳዘንኸኝ አይሉትም፤ የሐገርና የሕዝብን ኃላፊነት ቀብተው ሲያስረክቡት፤ ተግባሩ ተርታ፣ አስተሳሰቡ  መደዴ እንዳልኾነ ይታወቃል። ለተራ ሰው ዘውዱ ጌጥ ይመስለዋል፤ ላወቀው ግን አክሊለ ሶክ ነው” አልኩት፤ የከበደ ነገር እንደገጠመው ፊቱ ነግሮኛል፤ እኔ እናቱ እንጂ ሌላማ የርሱን ፊት አይቶ ክፌቱን አያውቅም። አያ ሆደ ባሕር።

በዚህ በሰማይ ቤት መድኃኒት ያጣሁለት በሽታዬ አንድ ልጄን ሲያዝን ማየት ብቻ ነው።

“እንዲያው ለመሆኑ አንቺና አቤቶ መጀመሪያ ቀን የት ነበር የተኛቻሁት? ከዚያስ በኋላ እንዴት ነበር የሚያገኙሽ?” አለኝ።

“አዮ ልጄ ለዚህ ነው ስግደትኽን፤ ጸሎትኽን አቋርጠኽ በጧት እዚህ የመጣኸው? ምነው ቀስ ብለህ ሲፈሰክ ይደርስ አልነበረ?” አልኩት። ዕውነትም በዚህ ወቅት አኗኗሩን የሚያውቅ ለዚህ ጥያቄ መልስ ፍለጋ እኔ ዘንድ ይመጣል ብሎ አይገምትም።

“ያለፈው እሑድ ለታ አንድ መልከ መልካም ሸጋ አንኮበር ያለ መስሎኝ ደንገጥ አልኩኝ፤ ወዲያው ደግሞ አጼ ምኒልክ ሲል፣ የያዝኩትን መጣፍ አስቀምጬ ደሞ ምን ሊለኝ ይሆን፤ በደግ የሚያነሳኝ ጠፍቷል ብዬ ማዳመጥ ጀመርኩ። ወዲያው የቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን፣ የቤተ መንግሥቱ ዙሪያ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል ብቅ አለ። ጉድ ብዬ እንደ ሕፃን አገጬ ስር ቁጭ አልኩ።”

“ስለ ዙሪያ ገባው፣ ስለ አልዩ አምባ፣ ስለ አንጎለላ ኪዳነ ምኅረት፤ ስለ ሁሉ አወጋና ስለ አንቺ ጀመረ።” አለና ንግግሩን ገታ አደረገ። ምናልባት መስማት የማልፈልግ ከኾነ እንዳስቆመው ሽቶ መሰለኝ።

“ምን አሉ፤ መቼም ያችኑ ገረድ ነበረችን ነው፤ ሌላ ምን ይላሉ፤” አልኩት እንደማይከፋበት ስለማውቅ።

“ኧረ ስምቼው የማላውቀው ሆኖብኝ ነው ካንቺ ለማረጋገጥ የመጣሁት፤” አለኝ ራሱን ዘንበል አድርጎ። የከበድ ያለ ነገር ሲያገኘው መሬት መሬት ነው እንጂ የሰው ፊት እያየ አያናግርም። አንቺ ምድር ፍረጂን ይል ይመስላል።

“አንተ የማታውቀው ታሪክ ከመቼ ወዲህ፤ ነው ከጊዜ ብዛት ረስተኸው?” አልኩት። ልጄ እንኳን ከእኔ ከእናቱ ሊገድሉት አቅደው ይዞ ካሰራቸው ጋር ተቀምጦ ታሪክ የሚጠይቅ ነበርና የማያውቀው ታሪክ፣ የሚዘነጋው ስም የለም። “እስቲ ጠይቀኝ?” ቸኮልኩ። “እስቲ ምን አሉ? እስቲ ጠይቀኝ፤ አንተ ጠፍቶህ እኔ የምመልስልኽን፤ ነው ጌታዋን አስከራ አብራው ተኛች አሉኝ” አልኩት።

“ኧረ መቼ እንደዚያ ኾነ፤ ከትለቁ ዋርካ ሥር ነው የተፀነስኽው አሉኝ እንጂ፤ ለመኾኑ እኔን ከመፀነስሽ በፊት ምን ያህል ጊዜ አብራችሁ ቆይታችኋል? ካልጠፋ ሥፍራስ ዛፍ ሥር ምን ወሰዳችሁ?” አለ።

“ኧረ ልጄ፤ እኔና አባትህ ያለ አንድ ቀን አልተገናኘንም፤ የመጀመሪያዬም የመጨረሻዬም አንዲት ዕለት ናት፤ አንተን የፀነስኩኽ ደግሞ ከዛፍ ሥር ሳይሆን ከትንሿ እልፍኛቸው ነበር፤ እኔስ እሺ እርሳቸው ከእልፍኛቸው ከውጡ በኋላ መች ሰው ተለይቷቸው ነው ዛፍ ስር የምንተኛው” አልኩት።

“እልፍኝ ውስጥ እንዴት አገኙሽ? ምን ታደርጊ ገባሽ?” አለኝ አላምነኝ ብሎ እንደመቆጣትም ከጅሎት።

“ልጄ፤ እኔ መጀመሪያ ከገበዙ ቤት ነበርኩ። እዚያ እያለሁ ሕልም አየሁና ነገርኳቸው። እርሳቸውም *አቤት ያንተ ሥራ* ብለው አምላካቸውን አድንቀው፤ *ልጄ ሆይ ካንቺ ትልቅ ሰው ይወጣል፤ ኢደራሽን ራስሽን በንጽሕና ጠብቂ፤ አምላክ ዕድሜ ከሰጠኝ ያሳየኝ ይሆናል፤ ይኸንን ለኔ የነገርሽውን ለሌላ እንዳትነግሪ፤* ብለው ከጥቂት ቀናት በኋላ ለእቴጌ *መልካም ሰው ናት፣ ምሥጢር ጠባቂ፣ ታማኝ፣ እግዜርን አክባሪ ናትና ለርስዎ ትሁንዎ* ብለው በአደራ አስረከቡኝ። ዕውነትም እቴጌ እንደ ልጅ እንጂ እንደ አገልጋይ አንድም ቀን ዝቅ አድርገውኝ አያውቁም። ከኔ በቀር ወደ ንጉሡም ሆነ ወደ አቤቶዎቹ እልፍኝ ዝር የሚል የለም ለዚያውም አለመኖራቸውን አረጋግጬ። ታዲያ እኔ ሁልጊዜ በልቤ እጠብቀው ስለነበረ መቼ ይሆን፣ ከማንስ ይሆን እያልኩ እጨነቅ ነበር። መምሕር ደግሞ ራስሽን በንጽሕና ጠብቂ ያሉኝ ይደውልብኝ ስለነበረ ተጠንቅቄ ነበር የምኖረው። ይኽ ጥንቃቄዬም ሳይሆን አይቀርም እቴጌን በጣም እንዲወዱኝ ያስገደዳቸው። ጊዜው ሲደርስ፣ የጥቅምት አቦን አክብረን በማግሥቱ እልፍኛቸውን እያነጠፍኩ አባትህ ከየት መጡ ሳይባል

---

[፩] መጽሐፈ መነኮሳት

ከች አሉ፤ ምድር ብትውጠኝ ደስ ባለኝ ነበር። እርሳቸውም ያለወትሯቸው ሲያዩኝ ደነገጡ። *ዛሬ እንዴት እማማ ለቀቀችሽ አሉኝ ገርሟቸው፤* የወጡ መስሎኝ ነበር አጠፋሁ ይማሩኝ አልኳቸው፤ *አንቺማ ምን ታደርጊ መውጣቴን አይተሽ ልታነጥፊ መጣሽ እኔ ነኝ እንጂ መጥቼ ያስደነገጥኩሽ፤ በሩን መለስ አድርጊው* አሉኝ። በፍርኃት በሩን መለስ አደረግሁት። ከዚያች ዕለት በኋላ አይናቸውን ማየት ስላልደፈርኩ ለማንጠፍ ስገባ እንኳን አሁንም አሁንም ብቅ እያልኩ እያየሁ ነበር። ያንኑ ዕለት አንተ ተፀነስኽ።" አልኩት አንድም ሳልዋሸው።

"ገበዙ እቴጌ ዘንድ ሲወስዱሽ ስለ ሕልምሽ አልነገሯቸውም?" አለኝ ግራ እየተጋባ።

"እኔ መቼም የተነጋገሩትን በሙሉ አላውቅም፤ ግን ነግረዋቸው ቢሆን መፀነሴን ሲሰሙ እንደዚያ አይቆጡም ነበር። ሆዴ መግፋቱን ሲያውቁ ጠርተው ጠየቁኝ ቀድመውም ከሚያዩት ከኹኔታዬ ጠርጥረው ነበርና። ከአቤቶ በሻህ ውረድ ነው ስላቸው ክው ነበር ያሉት። ሰምተው ቢሆን እንዲያ ይሆኑ አይመስለኝም፤" ብዙ መዘርዘሩን አልፈለግሁም።

"ይደንቃል፤ ልክ በቦታው ሆኖ ያደመጠም እንዲያ በድፍረት አይናገርም፤ ትንሽ እንኳን እፍረት ያልፈጠረባቸው። ስሙ የአማራ የባሕልና ታሪክ ባለሙያ የተባለ ጎልማሳ ነው፤ ፊደል መቁጠሩ ደግሞ አንዱ የሚለውን ሌላው ምን ይለዋል ብሎ እንዲያገናዝብ ነበር፤ ርጉም ማስያስና[፰] ጓደኞቹ የጻፉት ለልጆች ታሪክ እየተባለ ሊነገር ነውኮ በዚህ ዓይነት። ከርሱ ይልቅ እርሱ ለሚያስተምራቸው ሕፃናት አዝናለሁ። ይኸስ ተራ የግል ጉዳዩ ነው፤ ግን የሐገሪቱን ታሪክ እንዴት እያሉ ይሆን የሚያስተምሯቸው?" ብሎ መሬት መሬት እያየ፣ "እቴጌ ያውቁ ነበር፤ ግን እንድትወልጂ የፈለጉት ከሚያደሉለት ከአቤቶ ሠይፉ ነበር፤ አቤቶ ሠይፉ ሲነገራቸው ተጸይፈውሽ ለወንድማቸው ተዉላቸው። ወንድምየው ካንቺ ጋር ከዛፍ ሥር ተኙና እኔን ፀነስሽ፤ እያለ ሲናገር ጥርጣሬ እንኳን በፊቱ ላይ አይታይበትም፤" አለ ራሱን ወዝውዝ አድርጎ።

"ኧረ ጉድ ነው፤ አቤቶ ሠይፉ ልክ ልጅ ኢያሱ ደጃዝማች ተፈሪን ይቀናበት እንደነበረው ነበር አባትኽን የሚቀኑባቸው፤ የልጅ ኢያሱን ግን የሚያህል የለም። አጅሬ እንኳን ለወንድማቸው ሊተዉላቸው፤ ቢሰሙ ኖሮ የአንዲት ቀን ዕድሜ አይሰጡኝም፤ እናታቸውም ፊት ቢሆን አይምሩኝ፤" ፈገግ አለ አነጋገሬ እንዳይጠራጠር ከልቤ መኾኑ ገብቶት።

"ታዲያ የእቴጌን ቁጣ ማን አበረደልሽ?" ጭንቅ ብሎት።

"ፊታቸው ቆሜ እየተንቀጠቀጥኹ ስመልስላቸው፣ ፊታቸው በድንጋጤ ቀላ፤ አፋቸው ደርቆ መናገር ተሳናቸው፤ መቀመጫ ብለው እጥፍ አሉ፤ ትንሽ ቆዩና *ልጄ ውኃ ስጪኝ* አሉ። የዚህ ጊዜ ዕንባዬን እንደ ጅረት ውኃ አወረድኩት፤ አዋርጃቸው እንኳን ልጄ አሉኝ፣ አይንሽን አልየው ከፊቴ ጥፊ ይሉኛል ብዬ ነበር የምጠብቀው። *ምን ያስለቅስሻል አንቺ ዘለሽ ኢታንቂው እርሱ ነው እንጂ፤ ይልቅ ውኃ ስጪኝ* አሉኝ፤"

"አሁንም ልታለቅሺ ነው እንዴ? በቃ ተይው ይቅር፤ እኔም ትቼዋለሁ፤" አለ ሳግ ሲተናነቀኝ አይቶኝ።

"ውኃቸውን ተጎነጩና በረጅሙ ተነፈሱ፤ *አይ ቅዱስ ሚካኤል፣ እንዴት ታወጣኛለህ አሉ፤* ከርሳቸው ጋ ስለማልለይ ጃንሆይ እርሳቸው ሆን ብለው ያመቻቹት አድርገው የሚጠረጥሯቸው መሰሏቸውም እንደሁ እንጃ። በይ ከዚች ቤት እግርሽ እንዳትነቃነቅ አሉኝ። እሑዱን ምሳ ከተበላ በኋላ ጠሩኝና በዚያ የነበሩትን በሙሉ ለጊዜው ከጃንሆይ ጋር በምሥጢር የምነጋገረው አለኝ ብለዋል ብለሽ አሰናብቺያቸው አሉኝ። እንዳሉኝ አደረግኹ። ከዚያም ከጃንሆይ ፊት ቆመው ጌታዬ ጥፋት ተሰርቷልና ከሌላ ሰው ከሚሰሙት ከኔ ይስሙት ብዬ ነው አሉ። ጃንሆይም የተባለውን ጥፋት ጠየቁ፤ እቴጌ እኔን እየጠቆሙ ከአቤቶ በሻህ ውረድ ፀንሳለችና እርስዎ ፍርዱን ይስጡ ብለው አቀረቀሩ። ጃንሆይም ላፍታ ተመለከቱኝና፤ ለመሆኑ መቼ ነው ይኸ የኾነው ብለው ጠየቁ። እኔም የጥቅምት አቦ ማግሥት ብዬ መልስ ሰጠሁ። ጃንሆይም ሰው ሳይሰማ ወደ አንኮለላ ኪዳነ ምኅረት ትሄድና በዚያ ትቆይ፤ እዚህ እያለች ወሬው ከተሰማ አቤቶ ይጸማቀቅብኛል፤ ሌላ ሌላውን ጊዜው ሲደርስ እናከናውናለን አሉ። እኔም ወደዚያ ሔድኹ።"

"ማን ብለሽ ነበር የሰየምሽኝ?"

"ማን እልሃለሁ፤ እርሷ ኪዳነ ምኅረት የሰየመችህን ነዋ፤ ሣኅለ ድንግል፤"

"ሰዉስ ማን እያለ ነበር የሚጠራኝ?"

"ሰዉማ በተለይ ከቤት መንግሥት አካባቢ የሚመጡት ምኒልክ ነበር የሚሉህ፤ ገና ሳትወለድ በፊት *ምኒልክ የሚባል አንበሳ ከበሻህ ውረድ ይወለዳል* ብለው አንድ ባሕታዊ የሰኔ ሚካኤል ለታ ትንቢት ተናግረው ነበር። ግን በምሥጢር ያዙት ብለው ጃንሆይ አዘው ነበር፤ መፀነህን ሲሰሙ ይፋ አወጡት፤" አልኩት። "ያኔ በየሁለት ወሩ አይተኻት ና እየተባለ የሚላከው፤ እንዴት ነሽ፣ አይዞሽ፤ ብለውሻል ጃንሆይ እያለ የሚያጽናናኝ አንበርብርን ዛሬ የት ባገኘሁትና ከርሱ በሰማኸው።"

"ታዲያ ምን ይሁን ብሎ ነው *ምን ይልህ ሸዋ* ነበረ ስምህ፤ ብሎ ያ የአማራ የታሪክ ጎልማሳ ያወጋ የነበረው?" አለ ግራ ገብቶት።

"ምነው ባለፈ *ሰው አትግደል ጋላም ቢሆን* ብሏል አሉኝ ብለህ ስትበሳጭ አልነበር፤ ይኸም እንደርሱው ምን ላውራ ባይ ነው፡፡"

"ጎንደር በምርኮ ሳለሁ፤ ይኸ የባሪያ ልጅ ከኛ ከመኳንንቱ ልጆች ጋር ግብር የሚቀርበው ለምንድነው ይሉኝ ነበር። ይኽን ሲሰሙ ጃንሆይ ልጃቸው አልጣሽን ዳሩልኝና እረፉት አሏቸው። መሰደብን ቀምሼው ያለፍኩ ሰው ሌላውን ስሰድብ አምላክስ ዝም ይለኛል? ኧረ እያደር ጉድ ነው ጆሮ የሚሰማው።"

"ጃንሆይ ቴዎድሮስ እንኳን ልጃቸውን የዳሩልህ ስለወደዱህ እንዳይመስልህ፤ እርሳቸውም ትንቢቱን ስለሚያውቁ ነው። እግዜር ፈቃዱ ሳይሆን ቀረና ከአብራካችሁ ፍሬ አልተገኘም እንጂ።"

---

[፰] ማስያስ የሮማ ካቶሊክ መነኩሴ የነበረ ሲሆን በ፲፰፻፴፰ የጋላ ቪካሬት (ሐገረ ስብከት እንደማለት ነው) ቢሾፕ ("ሊቀጳጳስ") ኾኖ ተሾመ። በዚያ መርዙን ሲዘራ ለብዙ ጊዜ እየተባረረ ግን እየተመለሰ ይያዝ የነበረ ነው። ሙሶሊኒ የርሱ የስለላ መረጃዎች ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ከፍተኛውን አስተዋጽኦ ያበረከቱ እንደነበሩ መስክሮለታል።

“በይ የቀረውን ሲፈስክ ታወጊኛለሽ ለካ ብዙ የማላውቀው ብዙ የምትነግሪኝ ኖሮሻል? ሰላም ያስፈስከን” ብሎኝ ሔደ።

ሲፈስክ ሌላ ብዙ የምናወጋው ነበረንና ይኸ ጉዳይ አልተነሳም ከዚያም ወዲህ እንቶ ፈንቶ ነው ብሎም እንደሁ እንጃ አንስቶትም አያውቅ። አሁን በዚህ በጥምቀቱ በቃና ዘገሊላ ማግስት ከቅዳሴ መልስ አረፍ ብዬ ሳለሁ እቴጌ መጥተው ስናወጋ ይኸ ነገር ተነሳና እስከ ምሽት አብረን ቆየን። እርሳቸው ከተለዩኝ በኋላ ደግሞ በዚህ በመጪው የዐድዋ ድል በዓል አንዱ የባነነ እንዲሁ ያልሆነ ብሎ ያስከፋው ይሆን ብዬ ሰጋሁ። እናም እስቲ ለነዚያ ያኔ ዛፍ ሥር ተፀነሰ ያሉትን[፩] ከኔ ከባለቤቷ ይስሙ ብዬ ደስ ሳይለኝ ልናዘዘው ወደድኹ። ሌላ ጊዜ በድፍረት የሚናገረውም ትንሽ መስካሪ አለ ብሎ ይታቀባል፤ እበላ ባዩንም መጀመሪያ ከምንጩ ተነሳ ይሉት እንደሁ ብዬ።

**ገሪዲቱ የሣኅሌ እናት፤ እጅጋየሁ ለማ ነኝ ለትንሳኤው በሰላም አብሮ ያድርሰን።**

---

[፩] የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን